ዲሲ ደንብ ቁጥር 15-414

የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ምክር ቤት

እ.ኤ.አ ሚያዝያ 21/2004

በሕዝባዊ አገልግሎቶች ፕሮግራሞችና ተግባራት ውስን የሆነ የእንግሊዝኛ ችሎታ ያላቸውን ወይም ምንም ችሎታ የሌላቸውን ከዲስትሪክቱ የአስተዳደር ፕሮግራም መምሪያዎችና አገልግሎቶች ተጠቃሚ ለመሆን የሚጠይቁ ሰዎችን ተሳትፎ ለማሳደግ እና ጥያቄያቸውን ለማሟላት ሲባል የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የቃል ቋንቋዎች አገልግሎት የመስጠቱን አስፈላጊነት በመገምገም ይህንኑ አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን አገልግሎት ከሚሰጠው ወይም ሊሰጠው ከሚችለው ከጠቅላላው ነዋሪ መካከል ሦስት በመቶ ወይም አምስት በመቶ የሚያክሉት (አነስተኛ የሆነው ቁጥር ይወሰዳል) ግለሰቦች የእንግሊዝኛ ችሎታቸው ውስን የሆነበት ወይም ጭራሽ እንግሊዝኛ የማይችሉ የሆኑበት ሕብረተሰብ በሚኖርበት ጊዜ ከእንግሊዝኛ ውጭ ባለው ቋንቋ ሠነዶችን በጽሑፍ ተርጉሞ ያቀርባል:: የዲስትሪክቱ አስተዳደር ፕሮግራሞች ፣መምሪያዎችና አገልግሎቶች ጉልህ ከሆኑ የሕዝብ ግንኙነታቸው ጋር በተያያዘ የቋንቋ አገልግሎት እቅድ የሚነድፉበትና የሚያስፈጽሙበት እንዲሁም የቋንቋ አገልግሎት አስተባባሪ የሚሰይሙበት ዝግጅት መኖሩን ማረጋገጥ፣የሰብአዊ መብቶች ቢሮ የዲስትሪክቱ አስተዳደር ፕሮግራሞች ፣መምሪያዎች እና አገልግሎቶች ከዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ጋር የሚስማሙ መሆናቸውን ለመከታተል የማስተባበርና በበላይነት የመከታተል ሥራ እንዲሠራ እንዲሁም ለዚሁ ዓላማ የቋንቋ አገልግሎት ዳሬክተር እንዲሰይም መጠየቅ እንዲሁም እ.ኤ.አ የ1977ቱን የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የላቲን ማሕበረሰብ ልማት ደንብን ለማሻሻልና የሁለትዮሽ ቋንቋ አገልግሎቶች የትርጉም ደንብንና እንዲሁም ድግግሞሽ የፈጠሩ ድንጋጌዎችን ለማስቀረት::

ይህ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ምክር ቤት የሚያስፈፅመው ደንብ ሲሆን «የቋንቋ አገልግሎት ደንብ እ.ኤ.አ 2004 » ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

ክፍል 2 ፍቺ

በዚህ ደንብ ውስጥ የሚከተሉት ቃላት የሚከተለው ፍቺ ይኖራቸዋል::

1. «ተጠቃሚነት ወይም ተሳትፎ» ማለት አገልግሎት ሰጭ አካላት ስለሚሰጧቸው የሕዝብ አገልግሎቶች፣ ፕሮግራሞችና ተግባራት እንግሊዝኛ ተናጋሪ ከሆኑ

ግለሰቦች ባልተናነሰ መልኩ መረጃ እንዲያገኙና በነዚሁ አቅጣጫዎች እንዲሳተፉ ማስቻል ማለት ይሆናል፡፡

2. «አገልግሎት ሰጭ አካል» ማለት መረጃ ወይም አገልግሎት የሚሰጥ፣ፕሮግራም ወይም ሌሎች እንቅስቃሴዎችን በቀጥታ ለሕዝቡ የሚያከናውን ወይም ከሌሎች አካላት ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ውል በመፈፀም ፕሮግራሞችን፣ አገልግሎቶችን ወይም ሌሎች እንቅስቃሴዎችን የሚያስፈፅም ማንኛውም የዲስትሪክቱ አስተዳደር ኤጀንሲ ፣መምሪያ ወይም ፕሮግራም ማለት ይሆናል፡፡ «አገልግሎት ሰጭ አካላት» የሚለው መግለጫ አማካሪ የአካባቢ ኮሚሽኖችን የሚጨምር አይሆንም፡፡[*4689]

3. ሀ. «ከሕዝብ ጋር የሚያገናኛ ጉልህ ሥራ የሚያከናውኑ አገልግሎት ሰጭ አካላት» ማለት ከሕዝብ ጋር መገናኘት፣መዋዋልና መደራደር የሚጠይቅ ተቀዳሚ ኃላፊነት የተጣለባቸው አገልግሎት ሰጭ አካላት ማለት ይሆናል፡፡

ለ. ከሕዝብ ጋር የሚያገናኛ ጉልህ ሥራ ያላቸው አገልግሎት ሰጭ አካላት የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የአልኮል መጠጦች ቁጥጥር አስተዳደር
2. የጤና መምሪያ
3. የአእምሮ ጤና መምሪያ
4. የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ
5. የቅጥር አገልግሎቶች መምሪያ
6. የእሳትና ድንገተኛ የሕክምና አገልግሎቶች
7. የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የቤቶች ባለሥልጣን
8. የኮሎምቢያ ዱስትሪክት አጠቃላይ የአምቡላንስና የድንገተኛ ዕርዳታ ማዕከሎች
9. የድንገተኛ ሁኔታዎች አስተዳደር ኤጀንሲ
10. የከተማ ፖሊስ መምሪያ
11. የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሕዝብ ት/ቤቶች
12. የሞተር ተሽከርካሪዎች መምሪያ
13. የቤቶች የማሕበረሰብ ልማት መምሪያ

14. የሕዝባዊ ሥራዎች መምሪያ
15. የእርምት አገልግሎት መምሪያ
16. የእርጅና ቢሮ
17. የኰሎምቢያ ዲስትሪክት የሕዝብ ቤተመፃሕፍት
18. የመናፈሻዎችና የመዝናኛዎች መምሪያ
19. የተጠቀሚዎች የቁጥጥር ጉዳዮች መምሪያ
20. የልጆችና የቤተሰብ አገልግሎት ኤጀንሲ
21. የሰብአዊ መብቶች ቢሮ
22. የሠራተኞች ቅጥር ቢሮ
23. የፕላን ቢሮ
24. የውልና ግዢ ቢሮ
25. የቀረጥና የገቢ ቢሮ እንዲሁም
26. የሕዝብ ምክር ቤት ቢሮ

ሐ. ሌሎች ከሕዝብ ጋር የሚያገናኝ ጉልህ የሥራ ድርሻ ያላቸው የሥራ አካላት ከዲሲ የቋንቋ አገልግሎት ህብረት ጋር በመመካከር በክፍል 6 (ለ) (6) መሠረት በከንቲባው በኩል በቋንቋ አገልግሎት ዲሪክተሩ ይሰየማሉ፡፡

4. «የቋንቋ አገልግሎት ዲሪክተር» ማለት በሰብአዊ መብቶች ቢሮ ውስጥ በክፍል 6 መሠረት የዲስትሪክቱን ኤጀንሲዎች፣ዲፖርትመንቶችና ፕሮግራሞች ሥራ እየተከታተለ ከዚህ ደንብ ድንጋጌ ጋር መስማማቱን ለማረጋገጥ የሚያስተባብርና በበላይነት የሚከታተል ሹም ማለት ይሆናል፡፡

5. «ውስን የሆነ የእንግሊዝኛ ችሎታ ወይም እንግሊዝኛ አለማወቅ» ማለት እንግሊዝኛ ቋንቋን በበቂ መጠን መረዳታ አለመቻል ወይም በጽሑፍም ይሁን በቃል በእንግሊዝኛ ቋንቋ ሀሳብን መግለጽ አለመቻል ማለት ነው፡፡

6. «የቃል ቋንቋ አገልግሎቶች» ማለት የእንግሊዝኛ ችሎታቸው ውስን የሆነ ወይም ጨርሶ እንግሊዝኛ የማያውቁ ነዋሪዎች አገልግሎት ሰጭ አካላት በሚያከናውኗቸው ፕሮግራሞች ወይም አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ወይም እንዲሳተፉ ለማስቻል የሚሰጥ የቃል መረጃ አገልግሎት ዝግጅት [*4690] ማለት ነው፡፡ የቃል ቋንቋ አገልግሎቶች የሚለው መግለጫ ከሕዝብ ጋር በሚያገናኘው የሥራ ቦታዎች ሁለቱንም ቋንቋ የሚናገሩ ሠራተኞች ማስቀመጥን፣ ልምድ ያላቸውን የሰለጠኑ አስተርጓሚዎችን ማዘጋጀትን፣የስልክ ትርጉም አገልግሎት

ፕሮግራሞችን ማመቻቸትን፣ ከግል የትርጉም አገልግሎት ሰጪዎች ጋር መዋዋልን እንዲሁም በማሕበረሰብ አገልግሎት ድርጅቶች በሕዝብ ሂሣብ እየተደገፉ ለዚሁ ዓላማ የሚያገለግሉ አስተርጓሚዎች መጠቀምን የሚጨምር ይሆናል::

7. «መሠረታዊ ሰነዶች» ማለት መማልከቻዎች፣ ማስታወቂያዎች፣ የቅሬታ ቅጾች፣ ሕጋዊ ውሎች እንዲሁም ግልጽ በሆነ ይዘት ግለሰቦች ስለመብታቸው እንዲያውቁ ወይም ተጠቃሚ እንዲሆኑና ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚጠበቅባቸውን የሕጋዊነት መስፈርት ለማሳወቅ በአገልግሎት ሰጭ አካል የሚታተሙ ሌሎች ጽሑፎችን የሚያመለክት ይሆናል:: «መሠረታዊ ሰነዶች» የሚለው መግለጫ ከታክስ ጋር ግንኙነት ያላቸውን የትምህርትና በታክስ ገቢ ቢሮ የሚዘጋጁ ሌሎች ጽሑፎችን የሚጨምር ሲሆን የታክስ ቅጾችና መመሪያዎች አያካትትም::

ክፍል 3 በአገልግሎት ሰጭ አካላት የሚሰጥ የቃል ቋንቋ አገልግሎት

ሀ. አንድ አገልግሎት ሰጭ አካል ውስን የሆነ የእንግሊዝኛ ችሎታ ላለው ወይም በእንግሊዝኛ መግባባት ለማይችልና አገልግሎት ሰጭ አካሉ ከሚሰጠው አንድ አይነት አገልግሎት፣ፕሮግራም ወይም እንቅስቃሴ ተጠቃሚ ለመሆን ወይም በዚያ ለመሳተፍ ለሚፈልግ ሰው የቃል ቋንቋ አገልግሎት ይሰጣል::

ለ. አንድ አገልግሎት ሰጭ አካል ቢያንስ በየዓመቱ በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ የሚሰጣቸውን የቃል ቋንቋ አገልግሎቶች ይወስናል::

1. በኰሎምቢያ ዲስትሪክት የሚገኘው አገልግሎት ሰጭ አካል ያጋጠሙትን ውስን የእንግሊዝኛ ችሎታ ያላቸው ወይም በእንግሊዝኛ መግባባታ የማይችሉ አገልግሎት የተሰጣቸው ወይም ሊሰጣቸው የሚችሉ ሰዎች ቁጥር ወይም መቶኛ ብዛት፣

2. ውስን የሆነ የእንግሊዝኛ ችሎታ ያላቸው ወይም ጨርሶ በእንግሊዝኛ መግባባት የማይችሉ ሰዎች ወደ አገልግሎት ሰጭው አካል የሚመጡባቸውን አጋጣሚዎች ብዛት፣

3. አገልግሎት ሰጭ አካሉ የሚያከናውነው አገልግሎት ጠቀሜታ እንዲሁም፣

4. አገልግሎት ሰጭ አካሉ ያለው ጥሪት

ሐ. 1. አገልግሎት ሰጭ አካሉ በዚህ ክፍል ንዑስ ክፍል (ለ) ሥር በተገለፀው መሠረት የቃል ቋንቋ አገልግሎት አስፈላጊነቱን ለመወሰን የሚነገረውን ቋንቋ እና በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ የሚገኘው አገልግሎት ሰጭ አካል አገልግሎት የሰጣቸውን ወይም ሊሰጣቸው የሚችለውን በቂ የእንግሊዝኛ ችሎታ የሌላቸው ወይም ጨርሶ በእንግሊዝኛ መግባባት የማይችሉ ሰዎችን በተመለከተ ውህብ ለማግኘትና የሰዎቹን ቁጥር ወይም መቶኛ ብዛት ለማግኘት ከሚከተሉት የመረጃ ምንጮች ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፡፡

ሀ. የተባበሩት የአሜሪካን መንግሥት የሕዝብ ቆጠራ ቢሮ ወቅታዊ ሪፖርት «የቋንቋ አገልግሎትና የእንግሊዝኛ ችሎታ ቋንቋን መሠረት ያደረገ መገለል» (ወይም ሌላ ማንኛውም ተያያዥ ሪፖርት)

ለ. ከቋንቋው ጋር ተዛማጅነት ያለው ሌላ ማንኛውም መረጃ

ሐ. «ከአማካኝ መጠን በታች» እንግሊዝኛ የሚናገሩ ሰዎችን ለይቶ የሚጠቁም የቋንቋ ችሎታ የሚመለከት የሕዝብ ቆጠራ ውህብ

መ. የቋንቋ አጠቃቀምና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታን የሚመለከት አካባቢያዊ የሕዝብ ቆጠራ ውህብ

ሠ. አገልግሎት ሰጭ አካላት የሚያሰባስቧቸውን የግብአት ውህብ ጨምሮ ሌሎች የመንግሥት ውህቦች፣የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሕዝብ ት/ቤቶች የሚያሰባስቧቸው ውህቦች እንዲሁም ውስን የእንግሊዝኛ ችሎታ ባላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች መካከል ሥራቸውን የሚያከናውኑ የዲስትሪክቱ አስተዳደር ቢሮዎች እንዲሁም፣ ውስን የእንግሊዝኛ ችሎታ ባላቸው ማህበረሰብ ክፍሎችና በዲስትሪክቱ አስተዳደር መካከል እንደአገናኝ ሆነው የሚያገለግሉ እንደላቲን ጉዳዩች ቢሮና የእስያና የፖስፊክ ደሴቶች ጉዳይ ቢሮ የሚያሰባስቧቸውና [*4691] ይፋ የሚያደርጓቸው ውህቦች፡፡

ረ. የዲሲ የቋንቋ አገልግሎት ሕብረት የሚያሰባስበውና ይፋ የሚያደርገው ውህብ

2. አንድ አገልግሎት ሰጭ አካል ስለሚነገሩት ቋንቋዎችና በማህበረሰቡ ውስጥ የአንድ ቋንቋ ተጠቃሚ የሆኑ ውስን የእንግሊዝኛ ችሎታ ያላቸው ወይም ጨርሶ እንግሊዝኛ መናገር የማይችሉ በአገልግሎት ሰጭው አካል አገልግሎት የተሰጣቸው ወይም ሊሰጣቸው የሚችሉ ሰዎች ያላቸውን ቁጥር ወይም መቶኛ ብዛት በተመለከተ በየአመቱ ውህብ ያሰበስባል። አንድ አገልግሎት ሰጭ አካል ውህብና መነሻ ማመልከቻዎች ይህ ደንብ በክፍል 7 መሠረት ለአገልግሎት ሰጭው አካል ተፈፃሚ በሚሆንበት የአገልግሎት ዘመን ይህንን መረጃ የሚያካትቱበት ቦታ ይኖራቸዋል። የሰብአዊ መብቶች ቢሮ በበጀት እጥረት ምክንያት ይህ ተፈፃሚ ሊሆን እንደማይችል ከተገነዘበ አንድ አገልግሎት ሰጭ አካል በቀጣዩ የሥራ ዘመን መጀመሪያ ላይ ከዚህ አንቀጽ ጋር የሚስማማ ተግባር ለማከናወን አቅም የፈቀደውን ጥረት ሁሉ ያደርጋል። በዚህ ክፍል መሠረት የተሰበሰቡ መረጃዎች በሙሉ ለቋንቋ አገልግሎት ዲሪክተሩ ቀርበው በሚደርሰው ጥያቄ መሠረት በተቻለ ፍጥነት ለሕዝብ ይፋ ይደረጋሉ።

መ. አንድ አገልግሎት ሰጭ አካል በዚህ ክፍል ውስጥ ተለይቶ በተቀመጠው ውሣኔ መሠረት የቃል ቋንቋ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልገውን ተጨማሪ የሠራተኛ ኃይል ለማሟላት አገልግሎት ሰጭ አካሉ ባለው ከሕዝብ ጋር የሚያገናኝ ክፍል የሥራ ቦታ በጀት ሁለት ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ሠራተኞች ይቀጥራል።

## ክፍል 4 አንድ አገልግሎት ሰጭ አካል የሚሰጠው የጽሑፍ ቋንቋ አገልግሎት

ሀ. አንድ አገልግሎት ሰጭ አካል መሠረታዊ የሆኑ ሰነዶች ከእንግሊዝኛ ውጭ ወዳሉና በኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሚገኘው አገልግሎት ሰጭ አካል የሚሰጠው አገልግሎት ተጠቃሚዎች ወይም ወደፊት ተጠቃሚ ሊሆኑ ከሚችሉት የሕብረተሰቡ አካል መካከል ሦስት በመቶ ወይም በቁጥር 500 የሚሆኑት ግለሰቦች (ያነሰ ሆኖ የተገኘው ይወሰዳል) ውስን የእንግሊዝኛ ችሎታ ያላቸው ወይም ጨርሶ በእንግሊዝኛ መግባባት የማይችሉ በሆኑባቸው ቋንቋዎች የትርጉም አገልግሎት ይሰጣል።

ለ. የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች አገልግሎት ሰጭ ባልሆነ አካል ላይ የውል አስገዳጅነት ባህሪ በሚኖራቸው ጊዜ የዚህ ክፍል ንዑስ ክፍል ሀ ተፈፃሚ ይሆናል።

ክፍል 5 ከሕዝብ ጋር የሚያገናኝ ጉልህ ሥራ ያላቸው አገልግሎት ሰጭ አካላት የተጣለባቸው ተጨማሪ ግዴታ

(ሀ)(1) ከሕዝብ የሚያገናኝ ጉልህ ድርሻ ያለው አንድ አገልግሎት ሰጭ አካል በመተዳደሪያ ደንብ የሚመራ የቋንቋ አገልግሎት እቅድ ያወጣል::

2. እያንዳንዱ የቋንቋ አገልግሎት እቅድ ከቋንቋ አገልግሎት ዲሪክተሩ፣ ከዲሲ የቋንቋ አገልግሎት ሕብረት፣ ከአገልግሎት ሰጭ አካሉ የቋንቋ አገልግሎት አስተባባሪ እንዲሁም ውስን የእንግሊዝኛ ችሎታ ባላቸው ወይም ጨርሶ በእንግሊዝኛ መግባባት በማይችሉ ማሕበረሰቦች መካከል ከሚንቀሳቀሱ የኤጀንሲ ዳሪክተሮች ጋር በመመካከር የሚሠራ ይሆናል:: እያንዳንዱ የቋንቋ አገልግሎት እቅድ በየሁለት አመቱ የሚሻሻል ሲሆን ቢያንስ የሚከተሉትን ነገሮች ለይቶ የሚያስቀምጥ ይሆናል::

ሀ. የአገልግሎት ሰጭ አካሉ የሚሰጣቸው የቃል ቋንቋ አይነት እና እዚህ ውሣኔ ላይ የተደረሰበት መንገድ [*4692]

ለ. የአገልግሎት ሰጭ አካሉ የሚያቀርባቸው የተተረጐሙ ሰነዶች ርዕስና እዚህ ውሣኔ ላይ የተደረሰበት መንገድ

ሐ. የአገልግሎት ሰጭ አካሉ ከሕዝብ ጋር መገናኘት የሚጠይቁ የሥራ ደረጃዎች ብዛትና ከሕዝብ ጋር መገናኘት በሚጠይቁ የሥራ ደረጃዎች ላይ የተሰማሩ ሁለት ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ሠራተኞች ብዛት፣

መ. የሚሰጠው አገልግሎት ብቃት ግምገማ፣

ሠ. አገልግሎት ሰጭ አካሉ የቋንቋ አገልግሎት እቅዱን ለመተግበር እንደ ገቢ ምንጭ አድርጐ የሚያየው ሂሣብና በጀት መግለጫ::

3. የቋንቋ አገልግሎት እቅዱን በማውጣትና በማሻሻል ረገድ አገልግሎት ሰጭ አካሉ በክፍል 3(ሐ) (1) ላይ ከተጠቀሱት የውህብ ምንጮች ጋር ተመካክሮ ይሠራል::

ለ. ከሕዝብ ጋር የሚያገናኝ ጉልህ የሥራ ድርሻ ያለው አንድ አገልግሎት ሰጭ አካል የቋንቋ አገልግሎት አስተባባሪ የሚሰይም ሲሆን ይህ አስተባባሪ ተጠሪነቱ በቀጥታ ለአገልግሎት ሰጭ አካል ዲሪክተር ይሆናል እንዲሁም፣

1. ከቋንቋ አገልግሎት ዲሪክተሩ፣ከዲሲ የቋንቋ አገልግሎት ሕብረት እንዲሁም ውስን የእንግሊዝኛ ችሎታ ባላቸው ወይም ጨርሰው በእንግሊዝኛ መግባባት በማይችሉ ማሕበረሰቦች መካከል የሚንቀሳቀሱ የአስተዳደር ቢሮዎች ከኤጀንሲ ዳሪክተሮች ጋር በመመካከር የቋንቋ አገልግሎት እቅዱን ያወጣል እንዲሁም ያስፈጽማል። ከዚህ በተጨማሪ

2. በየጊዜው ለሕዝቡ አስቀድሞ በማስታወቅ ወቅታዊ ሕዝባዊ ስብሰባዎችን ያካሂዳል።

ሐ. ከሕዝብ ጋር የሚያገናኝ ጉልህ ድርሻ ያለው አንድ አገልግሎት ሰጭ አካል ውስን የእንግሊዝኛ ችሎታ ባላቸው ወይም ጨርሰው በእንግሊዝኛ መግባባት በማይችሉ ማሕበረሰቦች መካከል ስለቋንቋ አገልግሎት እቅዳቸውና በዚህ ደንብ መሠረት ስለሚያገኙት ጥቅምና አገልግሎት ጥናት ለማካሄድ የሚያስችል እቅድ ይነድፋል።

## ክፍል 6 የቋንቋ አገልግሎት ቁጥጥር፣ የቋንቋ አገልግሎት ዳሪክተር ተግባራት

ሀ. የሰብአዊ መብቶች ቢሮ አገልግሎት ሰጭ አካላት የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ለማስፈፀም የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በበላይነት ይከታተላል፣ በማዕከልነት ያስተባብራል እንዲሁም የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል። ከዚህም በተጨማሪ አገልግሎት ሰጭ አካል የሚሰጡት አገልግሎት የትርጉም ሥራን ወይም የአስተርጓሚነትን ተቀባይነት ያለው መስፈርት የሚያሟሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

ለ. በሰብአዊ መብቶች ቢሮ ውስጥ በዚህ ደንብ መሠረት የሚከናወኑ ተግባራትን የሚያስተባብር የቋንቋ አገልግሎት ዳሪክተር ይኖራል። የቋንቋ አገልግሎት ዳሪክተሩ:-

1. የእያንዳንዱ የቋንቋ አገልግሎት ሰጭ አካል እቅድ ከዚህ ደንብና እ.ኤ.አ ሐምሌ 2/1964 ከፀደቀው እ.ኤ.አ የ1964ቱ የፍ/ብሔር መብቶች ደንብ ክፍል 5 ጋር የሚስማማ መሆኑን ይቆጣጠራል:: (78 አን 252፣42 ዩ.ኤስ.ሲ. 2000ዲ. እስከ 2000ዲ. - 7)

2. የቋንቋ አገልግሎትን በተመለከተ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግ ከመሆኑም ሌላ በአገልግሎት ሰጭ አካላት ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ይመረምራል:: እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አገልግሎት ሰጭ አካሉ የቋንቋ አገልግሎትን በተመለከተ ሳያሟላው የቀረውን ጉዳይ በሚመለከት የደረሰበትን ውጤት በጽሑፍ ያሳውቃል:: ይህ የሚሆነው ይህንን የማድረጉ ኃላፊነት በአካባቢው የሰብአዊ መብቶች ቢሮ እየታየ ያለውን የግለሰቡን ቅሬታ ሂደት የሚያስተጓጉል እስካልሆነ ድረስ ብቻ ነው::

3. የቋንቋ አገልግሎት አስተባባሪዎቹ በዚህ ደንብ ላይ የተሰጣቸውን ኃላፊነት የሚያከናውኑበትን መንገድ ይገመግማል:: እንዲሁም ይቆጣጠራል [*4693]

4. ከቋንቋ አገልግሎት አስተባባሪዎች፣ ከዲሲ የቋንቋ አገልግሎት ሕብረትና ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ባላቸው ወይም ጨርሶ በእንግሊዝኛ መግባባት በማይችሉ ማሕበረሰቦች መካከል እንቅስቃሴ ከሚያካሂዱ የአስተዳዳር ቢሮ ኃላፊዎች ጋር በመመካከር ይሠራል::

5. ለሰብአዊ መብቶች ቢሮ የቋንቋ አገልግሎት አስተባባሪ ሆኖ ያገለግላል:: እንዲሁም

6. የአሠራር ደንብን በተከተለ መልኩ ከዲሲ የቋንቋ አገልግሎት ሕብረት ጋር በመመካከር በከንቲባው አማካይነት ተጨማሪ ከሕዝብ ጋር የሚያገናኝ ጉልህ የሥራ ድርሻ ያላቸውን አካላት ይሰይማል::

ክፍል 7 በምዕራፍ የተከፈለ አተገባበር

ሀ. ይህ ደንብ በሚከተሉት ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሚሆንበት ቀን አንስቶ ተግባራዊ ይደረጋል:-

1. የጤና መምሪያ

2. የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ

3. የቅጥር አገልግሎቶች መምሪያ
4. የከተማ ፖሊስ መምሪያ
5. የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሕዝብ ት/ቤቶች ሥርዓት
6. የፕላን ቢሮ
7. የእሳትና ድንገተኛ የሕክምና አገልግሎቶች
8. የሰብአዊ መብቶች ቢሮ

ለ. ይህ ደንብ እ.ኤ.አ ጥቅምት 1/2004 አንስቶ በሚከተሉት ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

1. የቤቶች የማሕበረሰብ ልማት መምሪያ
2. የአእምሮ ጤና መምሪያ
3. የሞተር ተሽከርካሪዎች መምሪያ
4. የልጆችና የቤተሰብ አገልግሎት ኤጀንሲ
5. የአልኮል መጠጦች ቁጥጥር አስተዳደር
6. የተጠቀሚዎች የቁጥጥር ጉዳዮች መምሪያ

ሐ. ይህ ደንብ እ.ኤ.አ ጥቅምት 1/2005 አንስቶ በሚከተሉት ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

1. የመናፈሻዎችና የመዝናኛዎች መምሪያ
2. የእርጅና ቢሮ
3. የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሕዝብ ቤተመፃሕፍት
4. የሠራተኞች ቅጥር ቢሮ
5. የውልና ግዢ ቢሮ
6. የእርምት አገልግሎት መምሪያ
7. የሕዝባዊ ሥራዎች መምሪያ እንዲሁም
8. የቀረጥና የገቢ ቢሮ

መ. ይህ ደንብ እ.ኤ.አ ጥቅምት 1/2006 አንስቶ በሁሉም የአገልግሎት ሰጭ አካላት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል 8 ተስማማሚ ማሻሻያዎች

ሀ. እ.ኤ.አ መስከረም 29/1976 አንስቶ ተፈፃሚ የሆነው የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የላቲን ማህበረሰብ ልማት ደንብ ክፍል 304 ተሽሯል፡፡ (ዲሲ ሕግ 1-86፣ዲሲ ኦፊሴል ኮድ 2-1314) [*4694]

ሰ. እ.ኤ.አ ከጥቅምት 26/1977 አንስቶ ተግባራዊ የሆነው የሁለት ቋንቋዎች ትርጉም አገልግሎት ደንብ ተሽሯል። (ዲሲ ሕግ 2-31፣ ዲሲ የኦፊሴል ኮድ 2-1342)

## ክፍል 9 የበጀትና የፋይናንስ እቅድ ተጨማሪ ክፍል

ይህ ደንብ ተፈፃሚ የሚሆነው በፀደቀ በጀትና የፋይናንስ እቅድ ውስጥ በሥራ ዘመኑ በሚኖረው ውጤት መሠረት ይሆናል። ይህ ደንብ ለድርሻ አካፋፈል መመሪያ ተገዢ ይሆናል።

## ክፍል 10 የሥራ ዘመን ውጤት መግለጫ

ምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ውጤት መግለጫውን በኮሚቴው ሪፖርት ውስጥ እ.ኤ.አ ታህሣሥ 24/1973 የፀደቀው የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የውስጥ አስተዳደር ደንብ ክፍል 602 (ሐ)(3) በሚጠይቀው መሠረት ያዘጋጃል። (87አን 813፣ዲሲ የኦፊሴል ኮድ 1-206.02 (ሐ) (3))

## ክፍል 11 ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ ደንብ በከንቲባው ከፀደቀ በኋላ (ወይም ከንቲባው ድምጽን በድምጽ የመሻር መብታቸውን በሚጠቀሙበት ጊዜ ምክር ቤቱ ይህንኑ ለመሻር እርምጃ ከወሰደ በኋላ)፣ እ.ኤ.አ ታህሣሥ 24/1973 የፀደቀው የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የውስጥ አስተዳደር ደንብ ክፍል 602 (ሐ)(1) (87አን 831፣ዲ.ሲ የኦፊሴል ኮድ 1-206.02 (ሐ)(1)) በሚጠይቀው መሠረት ለኮንግረስ ግምገማ የ30 ቀናት ጊዜ ካለፈ በኋላ እንዲሁም በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ሪጅስተር ታትሞ ከወጣ በኋላ ተፈፃሚ ይሆናል።

ሊንዳ ኤ ክሮፕ
ሊቀመንበር
የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ምክር ቤት
አንቶኒ ኤ ዊልያንስ
ከንቲባ
የኮሎምቢያ ዲስተሪክት
ፀደቀ
እ.ኤ.አ ሚያዝያ 21/2004